# የኢ.ህአዴግ ሥርዓትና የመልካም አስተዳደር “ሆድና ሆድ” ወይም “ጀርባና ጀርባ”

ይህንን ፅሑፍ እንድፅፍ ያነሳሳኝ በአዲሰ ፕሬስ ጋዜጣ ሰኔ 26 ቀን 2002 ዓ.ም “የኢ.ህአዴግ ሥርዓትና መልካም አስተዳደር ሆድና ጀርባ ” በሚል ርዕስ በጋዜጣው አዘጋጅ በርዕዮት አለሙ የተጻፈው ጽሑፍ ነው። አዘጋጇ የኢ.ፌዴሪ ህዝብ ዕንባ ጠባቂ ተቋም “መልካም አስተዳደርን ከማስፈን አንጻር የመገናኛ ብዙሃን ሚና ” ባዘጋጀው አውደ ጥናት ላይ ተቋሙ ላስተላለፈው ጥሪ አዎንታዊ ምላሽ ለመስጠትና ለዚህ በጎ ተግባር ድርሻዋን ለመወጣት እንደፃፈችው ገልጻለች። የጸሐፊዋ ሀሳብ ይህ ቢሆን ኖሮ መልካም ነበር። የፅሑፉ ይዘት፣ የአፃፃፍ ስነ-አመክንዮና ድምዳሜ ግን ይህ እንደሆነ የሚያረጋግጥ ስለመሆኑ አንዳችም አሳማኝነት የለውም። በመሆኑም እኔ ፅሑፉን ስመለከት የተሰማኝን ሃሳብ ከመፃፌ በፊት ስለኢ.ህአዴግ ስርዓት ምንነትና የመልካም አስተዳደር መርሆችን በማስቀመጥ ከጽሑፉ ይዘት፣ የአፃፃፍ ስነ-አመክንዮና ድምዳሜ ጋር ማነጻጸር የተሟላና ሚዛናዊ እይታ ለመያዝ ስለሚረዳ በዚሁ መጀመር መርጫለሁ።

በኢ.ህአዴግ ሥርዓት ለመጀመር የኢ.ህአዴግ ሥርዓት ማለት ኢ.ህአዴግ የሚመራው መንግስት የሚከተለው ስርዓተ-መንግስት (regime) ነው። ይህ ስርዓት ሲዘረዘር ኢ.ህአዴግ የኢ.ትዮጵያን ብሄሮች፣ ብሄረሰቦችና ህዝቦችን በእኩልነትና በመቻቻል ላይ በተመሰረተ አንድነት ወደ ልማት፣ ሰላምና ዴሞክራሲ ለማምራት በቀየሳቸው ፖለሲዎች የዘረጋው የአስተዳደር ዘይቤ ነው። ይህ የኢ.ህአዴግ ስርዓት በሀገራችን ለመጀመሪያ ጊዜ ህገ-መንግስታዊ ስርዓትን የዘረጋ፣ የመድብለ ፓርቲ ስርዓት ያረጋገጠና የአስተሳሰብና የእምነት ነፃነትንና ይህንኑ የመግለፅ መብት እንዲሁም የመደራጀት፣ ሰብአዊና ዴሞክራሲያዊ መብቶችን ያረጋገጠ ስርዓት ነው ማለት ይቻላል። በአስተዳደራዊ መስክም ያልተማከለ ፌዴራላዊ አስተዳደርን በኢ.ትዮጵያዊያን ማንነትና የዘመናት ጥያቄያቸው መልስ የሰጠ ስርዓት እውን ያደረገ ስርዓት ነው። የኢ.ህአዴግ ስርዓት የመልካም አስተዳደር ዋና መርህ በሆነው ያልተማከለ አስተዳደር ከማረጋገጡ በተጨማሪ በእነዚህ የአስተዳደር እርከኖች የሚፈፀሙ አስተዳደራዊ በደሎች ቢያጋጥሙ እንኳ ለማረም እንዲቻል የህዝብ ዕንባ ጠባቂ ተቋምንና የስነ-ምግባርና ጸረ-ሙስና ኮሚሽንን ማቋቋሙ ስርዓቱ ለመልካም አስተዳደር ምን ያህል ክብደት እንደሰጠ ማየት ይቻላል። ይህ ስርዓት ለዘመናት ሲበዘበዙና ሲረገጡ በኖሩት የብዙሃን ደሃ ጭቁን ህዝብ ልጆች መስዋዕት ውጤት የተመሰረተ በመሆኑ የመልካም አስተዳደር የመኖርና ያለመኖር የሞት የሽረት ቁልፍ ጉዳይ መሆኑንም ያምናል።

ኢ.ህአዴግ የሚመራው ስርዓተ-መንግስት (regime) በተለይ በፖለቲካ፣ በኢ.ኮኖሚና በማህበራዊ አገልግሎቶች ለዘመናት ተረስተው የኖሩትን ጭቁን ብሄሮች፣ ብሄረሰቦችና ህዝቦችን፣ ሰፊውን አርሶ አደር፣ አርብቶ አደርና ደሃውን የከተማ ነዋሪ ተጠቃሚ ለማድረግ በዘረጋው መልካም አስተዳደር ሁሉንም መንግስታዊ አገልግሎቶች አቅም በፈቀደ መጠን በሁሉም አካባቢ.ዎች በፍትሃዊነት ለማዳረስ ጥረት በማድረግ ላይ ይገኛል። የኢ.ህአዴግ ስርዓት ስለ መልካም አስተዳደር መርሆዎች በሥነ-ዜጋና ሥነ-ምግባር ትምህርት ከመጀመሪያ ደረጃ እስከ ዩኒቨርሲቲዎች ድረስ በመስጠት መርሆዎቹን በትክክል የተገነዘበ ለተግባራዊነታቸው በፅናት የሚቆም በሚሊዮኖች የሚቆጠር ዜጋ በማፍራት ላይ ያለመሆኑንና በዩኒቨርሲቲዎች መልካም አስተዳደር ትምህርት

ራሱን ችሎ በዲግሪ መስጠት መጀመሩን ፀሐፊዋ ለምን እንዳላየችው ጥያቄ ያስነሳል። ስለ ኢህአዴግ ስርዓት ይህንን ያህል ካልኩ ወደ መልካም አስተዳደር መርሆዎች ላምራ።

የመልካም አስተዳደር መርሆዎች በተለያዩ የአለም አቀፍ ተቋማትና ምሁራን በተለያየ መልኩ ቢገልፁም ዋና ዋናዎቹ ፅንሰ ሀሳቦች ተሳትፏአዊነት፣ ግልፅነት፣ የህግ-የበላይነት፣ ተጠያቂነት፣ ቶሎ ምላሽ መስጠት፣ ፍትሐዊነት፣ የጋራ መግባባት፣ ቀልጣፋነትና ውጤታማነት ናቸው። እነዚህን መርሆች ከኢህአዴግ ስርዓት ጋር መፈተሽ ስለ ፅሑፉ አንድምታ በቂ ምላሽ ስለሚሰጥና እኔም መልካም አስተዳደር በሀገራችን እንዲሰፍን የበኩሌን ድርሻ ለመወጣት ስለሚረዳኝ እንደሚከተለው ለማቅረብ እሞክራለሁ።

ኢህአዴግ በ1995 አምስተኛው ድርጅታዊ ጉባኤው ላይ መልካም አስተዳደርን በሚመለከት ውሳኔ አስተላልፏል። እንዲሁም በ1997 ዓ.ም በተካሄደው ስድስተኛው ድርጀታዊ ጉባኤ መልካም አስተዳደር በሚመለከት በ5ኛው ድርጅታዊ ጉባኤ የተላለፈውን ውሳኔ አፈፃፀም በመገምገም በመልካም አስተዳደር ስር ነቀል ለውጥ እንዲመጣ ዳግም ውሳኔ አስተላልፏል። ይህንን ተከትሎ ከላይ የተጠቀሱትን የመልካም አስተዳደር መርሆችና ድርጅታዊ ውሳኔዎችን ተግባራዊ ለማድረግ በ1999 ዓ.ም የመልካም አስተዳደር ፓኬጅ ተቀርፆ ተግባራዊ እየተደረገ ይገኛል። ይህ ፓኬጅ በገጠር ወረዳና ቀበሌ የመልካም አስተዳደር ጥያቄ የሚልና በተጠቀሱት የአስተዳደር እርከኖች የመልካም አስተዳደር መፍትሔዎችን የያዘ ሰነድም በ1999 ዓ.ም በአቅም ግንባታ ሚኒስቴር ታትሞ በተግባር ላይ እየዋለ ይገኛል። እነዚህ ተግባራት ከመሰረታዊ የአሰራር ለውጥ ጋር ተጣምረው አበረታች ውጤት እያስመዘገቡ ቢሆንም አሁንም ያልተቀረፉ ችግሮችን ስር ነቀል በሆነ ሁኔታ ለመፍታት በየደረጃው ሰፊ ስራ እየተሰራ ነው።

በመሰረቱ አንድን ፖሊሲ ለማስፈፀም ስተራቴጂ ከማውጣት ቀጥሎ ትግበራውን ተግባራዊና ተጨባጭ ለማድረግ ፓኬጅ ቁልፍ መሳሪያ መሆኑ ይታወቃል። ከዚህ በመነሳት ኢህአዴግ በመልካም አስተዳደር ለማስፈን ስር ነቀል ለውጥ በተጨባጭ ለማምጣት ምን ያህል ትኩረት እንደሰጠ መገንዘብ ይቻላል።

የኢህአዴግን ስርዓትና የመልካም አስተዳደር መርሆዎችን በተመለከተ ከላይ የተጠቀሱትን ለመንደርደሪያ ያክል ካስቀመጠኩኝ በኋላ ወደ ፅሑፉ መልስ ለመግባት እሞክራለሁ።

ከፅሑፉ የይዘት መከራከሪያ ለመነሳት ፀሐፊዋ የመከራከሪያ መንደርደሪያዎች 1ኛ. የኢፌዴሪ የህዝብ ዕንባ ጠባቂ ተቋም የቀድሞ ኃላፊ ከተቋሙ ጋዜጣ ጋር የተቋሙን የአመሰራረት አስፈላጊነት በተመለከተ ያደረጉት ቃለ ምልልስ፣ 2ኛ. የህዝብ ዕምባ ጠባቂ ተቋም “መልካም አስተዳደርን ከማስፈን አንፃር የመገናኛ ብዙሃን ሚና” በሚል ተዘጋጀ በተባለው የምክክር አውደ ጥናት ላይ በአቶ አህመድ ዑመር የቀረበ ጥናታዊ ፅሑፍ ከአለም ባንክ በመዋስ ለመልካም አስተዳደር የሰጠው ፍች፣ 3ኛ የህዝብ ዕንባ ጠባቂ ተቋም ያሰራጨው ፅሑፍ ላይ የመልካም አስተዳደር ትርጉም ተብለው የተጠቀሱት ናቸው በዋናነት ፀሐፊዋን የኢህአዴግ ስርዓትና መልካም አስተዳደር ሆድና ጀርባ የሚያስበል መደምደሚያ ላይ እንድትደርስ ያደረጉት። እንዲሁም ይህን መንደርደሪያና መደሚደሚያ ይዛ ነው ፀሐፊዋ ለመልካም አስተዳደር መስፈን የበኩሉን ለመወጣት የተነሳው ማለት ነው። ፅሑፉ ስለ ኢህአዴግ ስርዓትና ስለ መልካም አስተዳደር መርሆዎች አንዳች መንደርደሪያ አላነሳም። እነዚህን መሰረታዊ ነገሮችን ሳያነሳ ሆድና ጀርባ መሆናቸውን እንዴት እንዳረጋገጠ የሚያውቀው እሱ ብቻ ነው።

በመሰረቱ የዚህ ፅሑፉ የይዘት መንደርደሪያና ድምዳሜ በመሰረቱ የኢህአዴግ ስርዓት ምን እንደሆነና ምን ውጤት በአዎንታና በአሉታ ያመጣውን አንደምታ አንድም ሳይጠቅስ ግልብ ድምዳሜ ላይ በመድረሱ የተሳሳተ ብቻም ሳይሆን የኢህአዴግ ስርዓት በዘረጋው አስተዳደርና በቀረፀው የመልካም አስተዳደር ፓኬጅ ውጭ ምናልባት ሊፈፀሙ የሚችሉት አስተዳደራዊ በደሎች ለማረምና እርምጃ ለመውሰድ ስርዓቱ በፈጠረው ተቋም መስፈርት የኢህአዴግን ስርዓት መልሶ መለካት በምንም ስነ-አመክንዮ ተቀባይነት የለውም። ስለሆነም የፅሑፉ መንደርደሪያ የሸቀ ንፅፅር (weak analogy) መደሚደሚያው ደግሞ ግልብ (Hasty generalization) በመሆኑ በምንም ስነ-አመክንዮ (logic) ወደ እውነትና አሳማኝነት አያመራም። በመሰረቱ የዚህ ፅሑፍ ሀሳብ በ2002 ዓ.ም ምርጫ ወቅት ያልተማከለ አስተዳደር በሚመለከት በፓርቲዎች መካከል በቀረበው ክርክር ላይ ተቃዋሚዎች ያቀረቡት ሀሳብና በህዝብ ድምፅ የተሸነፈ ሃሳብ ነው። በተጨማሪም የኢህአዴግን ስርዓት በመልካም አስተዳደር ለመለካት ፀሐፊዋ የተነሳችበት መንደረደሪያ ቁንፅል፣ የተጠቀመው ማሳያ ምሳሌዎች ያለአግባብና በተገቢው የህግ መነፅር ያለተቀኙና ያስቀመጠችው መደምደሚያ ፈፅሞ የኢህአዴግን ስርዓት የማያሳይ ሆኖ ጉዳዩን በዝርዝር ማየት ብዙም ባያስፈልግም የፅሑፉም የይዘት መከራከሪያ ዝርዝር ማየቱ ስለ መልካም አስተዳደር የተስተካከለ ግንዛቤ እንድንይዝ ስለሚረዳና ከዚህ አንፃር መሰረተ ቢስነቱንም ስለሚያረጋግጥ አንድ በአንድ እንደሚከተለው እንመልከት።

አንደኛ "ለሚወስዳቸው እርምጃዎች ተጠያቂ የሚሆን መንግስት" ከሚለው ሀረግ (አቶ አህመድ ዑመር) እንደምንረዳው መልካም አስተዳደር ያለው መንግስት ቢያጠፋ ሊጠየቅ የሚችል መሆኑን ፀሐፊዋ ጠቅሳ ኢትዮጵያ ለዚህ እንዳልታደለችና " ንጉስ አይከሰስም ሰማይ አይታረስም " የሚለው አባባል ዛሬም በተግባር ላይ እንዳለ በፅሑፉ ተቀምጧል ። ለዚህ መንግስት ተጠያቂ አለመሆኑን ለማሳየት የተጠቀመው ማሳያ በ1997ቱ ምርጫን ውጤትን በተመለከተ ምርጫ ቦርድ ያወጣውን መግለጫ ተከትሎ "ድምፃችን ተነጥቋል" በማለት በወቅቱ አደባባይ የወጡ ሰላማዊ ሰልፈኞች ላይ የመንግስት እርምጃ ይገኝበታል በማለት ፀሐፊዋ አስቀምጣለች።

ይህ ሀሳብ መንግስት እንደማይጠየቅ ለማሳየት የቀረበ ሀሳብ ነው። ይህ ሀሳብ በመሰረቱ ከመልካም አስተዳደር መርሆዎች ውሰጥ የህግ የበላይነትን የሚፃረርና የመንግስትን የህግና ስርዓት የማስከበር ኋላፊነት (ተጠያቂነትን) የማይቀበል ነው። በተጨማሪም ሀሳቡ ህግና ስርዓት ለመልካም አስተዳደር አልፋ- ኦሜጋው መሆኑንም የሚክድ በመሆኑ ህግ-መንግስታዊ ስርዓትን በአመፅና በነውጥ ለመናድ 15 ሺ ሕይወት ከፍለን ቤተ መንግስት እንገባለን ተብሎ የተጠራውን ህገወጥ ሰልፍ "ሰላማዊ ሰልፍ" ብሎ ማስቀመጡ ፅሑፉ በእውቀት ላይ ያልተመሰረተ መሆኑን በግልፅ ያሳያል።

ሁለተኛው ሀሳብ "ሁሉም አካላት በህግ የበላይነት የሚያምኑ የሚንቀሳቀሱበት ስርዓት" የሚለው ሀረግ (አቶ አህመድ ዑመር) ስንወስድ በተመሳሳይ ሁኔታ በሀገራችን በስራ ላይ ያልዋለ መሆኑን እንገነዘባለን በማለት ፀሐፊዋ ታስቀምጣለች። ለማሳያነት ጠቅላይ ሚኒስትሩ ከምርጫው በፊት መጋቢት 9 ቀን ባደረጉት ንግግር በተቃዋሚዎች ላይ መረጃ እየሰበሰቡ እንደሆነና ከምርጫው በኋላ አስፈላጊ ሆኖ ሲገኝ ወደ ፍርድ ቤት እንደሚያመሩ ገልፀው ነበር ይልና፤ ምርጫው ካለፈ ግንቦት 17 ቀን ደግሞ "መንግስት ለህዝብ ድምፅ ክብር ለመስጠት ያለፈውን እንዳለፈ ቆጥሮ ወንጀለኞችን ከማሳደድ ይቆጠባል" ማለታቸውን ፀሐፊዋ ወስዳ "ሰውዬው የሀገሪቷን ህግ አተገባበር ኢ-ተጨባጭዊ እንዲሆን አድርገዋል" ብላ አስቀምጣ በመልካም አስተዳደር ፍችና ከሀገሪቷ ነባራዊ ሁኔታ ጋር ያለው ተቃርኖ ግልፅ ይሆንልናል በማለት ሀሳቧን ትደመድማለች።

በተጨማሪ ፀሐፊዋ የሰዎችን የመከሰስና አለመከሰስ የሚወስኑት የኢህአዴግ ሊቀ መንበር ናቸው ወይ ብላ ትጠይቃለች።

ለዚህ የሀሳብ መከራከሪያ ምላሽ ለመስጠት ፅሑፉ በጥያቄ መልክ ያስቀመጠውና የደረሰበት መደምደሚያ የጠቅላይ ሚኒስተሩን መንግስታዊ ስልጣን የማይቀበል ከመሆኑም ሌላ ንግግራቸውንም አለአግባብና ያለቦታው የደነቀረ ነው። ይህም የሚያሳየው የጠቅላይ ሚኒስትሩ የመጋቢት 7 ቀን ንግግራቸው “አስፈላጊ ሆኖ ሲገኝ “ የምትለዋን ሀረግና የቀለም አብዮተኞችን የአጣብቅኝ ስልት አካሄድና የመንግስትን ህግና ስርዓት የማስከበር ስልጣን ያላገናዘበ ነው። ለዚህ ተጨባጭ ማሳያ ደግሞ “ሰውዬው የሀገሪቷን ህግ አተገባበር ኢ-ተጨባጫዊ እንዲሆን ማድረጋቸው ------” የሚለው ሀረግ መንግስታዊ ስልጣናቸውን በመግፈፍ “ ሰውዬው” ብሎ ህግ አይገዛቸውም ለማለት ፀሐፊዋ ያለአግባብ የጠቅላይ ሚኒስትሩን ስልጣናዊ ቃል በመካድ ምንም መንግስታዊ ስልጣን የሌለው ሰው በማስመሰል ለሾቀ ንፅፅር (weak analogy) መጠቀሟን ያሳያል።

በመሆኑም ይህ የፀሐፊዋ ማሳያም ከላይ እንደ ተጠቀሰው ሁሉ መሰረተ ቢስ መንደርደሪያና ያለአግባብ  የተቀመጠ መደምደሚያ ከመሆኑም ሌላ ስለ መልካም አስተዳደር ማስፈን ሳይሆን መልካም አስተዳደርን የማንኳሰስ ተልዕኮ ያለው ሀሳብ ነው።።

በሶስተኛነትና አራተኛነት ፀሐፊው የምርጫ ቦርድ ገለልተኛነትና የሲቪል ማህበራት ተሳትፎ የመልካም አስተዳደር መገለጫዎች መሆናቸውን አቅርቦ  የቦርዱ ገለልተኝነት በጥያቄ ውስጥ እንደሆነና የሲቪል ማህበራትም ለኢህአዴግ የፖለቲካ መጠቀሚያነት እንደሚውሉ ያትታል። ፅሑፉ በመሰረቱ በ1997 ዓ.ም የተካሄደውንም ምርጫ ውጤት በሚመለከት ምርጫ ቦርድ የሰጠውን መግለጫ በመቃወም ህግና ስርዓትን በአመፅና በነውጥ ለመናድ የወጡትን ህገ ወጥ ሰልፈኞችን “ሰላማዊ ሰልፈኞች ” በማለት ማስቀመጡ  ህጋዊ ስርዓትን የሚፃረር በመሆኑ ስለ መልካም አስተዳደርና ሰለምርጫ ቦርድ ገለልተኝነት የማስረዳት የሞራል ብቃት የለውም። ስለሆነም ሀሳቡ ላይ ጊዜ ማጥፋት አያስፈልግም።

ሲቪል ማህበራትንም በሚመለከት ኢህአዴግ የሚመራው መንግስት የሚከተለው መርህ ተቋማቱ የሀገሪቷን ህግና ስርዓት መሰረት የሀገሪቷን ጥቅም በማይጎዳና በመልካም አስተዳደር መርህ እንዲንቀሳቀሱ ነው። ይህ ማለት በተጠያቂነትና በግልፅነት እንዲንቀሳቀሱ ማድረግ ነው። በውስጡ በግልፅነትና በተጠያቂነት ተንቀሳቅሶ መልካም አስተዳደርን ያላሰፈነ ሲቪል ማህበር የመልካም አስተዳደር ተዋናይ ሊሆን አይችልም። መንግስት ደግሞ በኢትዮጵያዊያን ህዝብ ስም የተሰበሰበው እርዳታ በግልፅነት ለታለመለት ዓላማ መዋሉን የማረጋገጥ ኃላፊነት አለበት።

በዋናነት ፅሑፉ በዚህ ሀሳቡ መንግስትንና ኢህአዴግን ለያይቶ ያለማየት ችግር ወደ ትክክለኛ መደምደሚያ እንዳይደርስ ያደረገው ይመስላል።

በመቀጠል ፅሑፉ “ለህግ ተገዥ የሆነ አስፈፃሚ ሳይሆን በሀገራችን ያለው የተገላቢጦሽ ነው” በማለት ይደመድምና ለማሳያ የወ/ሪት ብርቱካንን የመጎብኘት መብት ፍ/ቤት ቢያስተላልፍም ማረሚያ ቤቱ በእምቢታው እንደፀና ነው በማለት ፀሐፊዋ የአስፈፃሚው አካል ለህግ ተገዥ አለመሆን ለማሳየት ተጠቅማበታለች።

ጉዳዩን በሚመለከት ወ/ሪት ብርቱካን በዘመዶቿ እየተጎበኘች እንደሆነ የመንግስት ኮሙዩኒኬሽን በተደጋጋሚ ሲገልፅ መቆየቱ ይታወቃል። በፅሑፉ አስፈፃሚው አካል የህግ የበላይ መሆኑን

ለማሳየትም ሆነ አካሉም ማን እንደሆነ በትክክል ለመግለፅ የተቀመጠ አንዳች ጭብጥ የማይታይበት በመሆኑ አሳማኝነት የለውም። ከዚህ ይልቅ የወ/ሪት ብርቱካንን እስራት ለጥላቻ ፖለቲካ ፍጆታ ለመጠቀም ሲራገብ የነበረውን አዝማሚያ  ፀሐፊዋ እውነትን በማውገርገርና በማፋለስ ለመጠቀም መፈለጓን ነው የሚያሳየው።

ፀሐፊዋ "እውነተኛና ኃላፊነት የሚሰማው ነፃ ፕሬስ" በሚል በተጠቀሰው ፅሑፍ የተቀመጠውን የመልካም አስተዳደር ፍች በሚመለከት መንግስት ኃላፊነት በማይሰማቸው ፕሬሶች ላይ የወሰደውን እርምጃ ኢ.ህአዴግ ወሰደ በማለት ሁለቱን አንድ አድርጋ የማየት ችግሯን አሁንም ከመድገሟም ሌላ ለምን እርምጃ ተወሰደባቸው የሚለውን አትመልስም።

ፅሑፉ ከተነሳበት ዓላማ አንፃር ማለትም "መልካም አስተዳደርን ከማስፈን የመገናኛ ብዙሃን ሚና" በሚመለከት እውነተኛና ኃላፊነት በሚሰማው ነፃ ፕሬስ ላይ ማተኮር ሲገባው በዚህ ጉዳይ ላይ አንዳችም ጭብጥ ሳያስቀምጥ ማለፉ የተነሳበትን ዓላማ መሳቱን ፕሬስን በሚመለከት የተቀመጠው የይዘት ስፋትና አግባብ ራሱ ምስክር ነው።

የእንባ ጠባቂ ተቋምን ተአማኒነት ጥያቄ ውስጥ እንደሆነ ፀሐፊው ይጠቅስና ለዚህ ምክንያት ብሎ አስተያየት ሰጪዎች የኢ.ህአዴግ በሁሉም ቦታ ለመገኘት የመፈለግ አካሄድ አንፃር ተቋሙን እንደገለልተኛ መውሰድ እንደሞኝነት ይቆጥሩታል ይላል። የተቋሙ የትምህርትና ስልጠና ቡድን መሪ ጉዳዩን በሚመለከት በተጠቀሰው አውደ ጥናት ላይ ተቋማቸው ተጠሪነቱ የብዙ አባላት ስብስብ ለሆነው ለህዝብ ተወካዮች ም/ቤት በመሆኑ ነፃ ለመባል የሚያበቃ መሆኑን ማስረዳታቸውን ትንታኔ እውነት አድርገን ወስደን  አሁን ምርጫ ቦርድ በተገለፀው ውጤት መሰረት ኢ.ህአዴግ 99.6% የፓርላማ ወንበሮችን በማሸነፉ የተቋሙ ጥያቄ ምልክት ውስጥ መግባቱን ያሰቀምጣል ፅሑፉ። ፅሑፉ የህዝብ እንባ ጠባቂ ተቋም ኢ.ህአዴግ የሚመራው መንግስት መልካም አስተዳደርን በተሟላ መልኩ ለመፈፀም ያቋቀመው ተቋም መሆኑንም በግልፅ ይክዳል ብቻም ሳይሆን ማንኛውም ተቋም ህዝብ የመረጠውና በፓርላማ አብላጫ ድምፅ ባገኘው ፓርቲ ከሚመሰረተው መንግስት ቁጥጥር ውጭ ካልሆነ ገለልተኛ አይደለም ይላል። ይህንን ያለበት ምክንያት በምን ስነ-አመክንዮ እንደሆነ እንቆቅልሽ ብቻም ሳይሆን የመልካም አስተዳደር መርሆች ውስጥ በህዝብ የተመረጠ መንግስት ተጠያቂነትንና የመንግስትን ስልጣን ያላገናዘበ ነው።

ለማጠቃለል የፅሑፉ  መንደርደሪያ በቁንፅል ሃሳብ ላይ የተመሰረተ፣ የቀረቡት ማሳያዎች ያለአግባብ የቀረቡ፣ የመልካም አስተዳደርን መርሆች ያላገናዘቡና ህገ-መንግስታዊ ስርዓትን በሚፃረር መልኩ የቀረቡና መደምደሚያው ደግሞ በእውቀት ላይ ያልተመሰረተና እርስ በርሱ የሚጣረስ በመሆኑ የኢ.ህአዴግ ስርዓትንና መልካም አስተዳደርን ሆድና ጀርባ መሆናቸውን ፈፅሞ አያሳይም። ፅሑፉ ስለ ሁለቱ ጉዳዮች አንዳች የእውቀት ጭብጥ የሌለውና ተጨባጭ ሁኔታዎችን ያለቦታቸው በመሰንቀር ከአግባብ ውጭ በማውገርገር፣ በማፋለስና በመካድ የተፃፈ ነው።
እውነታው የአህአዴግ ስርዓት በሀገራችን መልካም አስተዳደርን ስር ነቀል በሆነ ሁኔታ ለማስፈን ሰፊ ጥረት በማድረግ ላይ መሆኑ ነው።
የሀገራችን ህዝቦችም በዘንደሮው ምርጫ ኢ.ህአዴግን በከፍተኛ ድምፅ የመረጡት ኢ.ህአዴግ መልካም አስተዳደርን ለማስፈን ያደረገውን ከፍተኛ ትግል በመደገፍ ነው። በልማቱ መስክም ኢ.ህአዴግ ከፍተኛ ለውጥ ማምጣቱን ፀሐፊዋ አይክዱትም።ልማት ደግሞ ያለ መልካም አስተዳደር አይታሰብም።

በመሆኑም የፃፊዋን የመተቸት መብት ባከብርም ኢ.ህአዴግ ለመልካም አስተዳደር መስፈን ያደረገውን ርብርብ ከአጠቃላይ መይቀፍ ውጭ የሚገመግም በመሆኑ የአገራችን ተቋሚዎች የተከተሉት የውድቀት አቅጣጫ የተከተለ ነው።

አዲስ ፕሬስ ጋዜጣም እንዲህ ዓይነቱን ጭፍን ነቀፌታ ያዘለ ፅሑፍ ማስተናገዱም በአገራችን መልካም አስተዳደርን ለማስፈን የሚካሄደውን ርብርብ እንደብዙዎቹ የግል ጋዜጦች በተንሸዋረረ ዓይን የሚመለከተው መሆኑን የሚያሳይ ነው።

ለማንኛውም የኢ.ህአዴግ ስርዓትና መልካም አስተዳደር ግንኙነት በተመለከተ የፀሐፊዋን ቃላት በመጠቀም ሆድና ጀርባ ሳይሆን "ሆድና ሆድ" ወይም "ጀርባና ጀርባ " ነው ማለት ከእውነታው ብዙም የሚርቅ አይመስለኝም።

ቸር እንሰንብት ሁሉም ዜጋ መልካም አስተዳደርን ስር ነቀል በሆነ ለማስፈን በሚደረገው ትግል የየሚናቻችንን እንወጣ መልዕክቴ !ባይ! ባይ !

ቃልቤሳ ዳምቅሳ (የኢ.ህአዴግ አባል) ነኝ ከመሃል ኢ.ትዮጵያ አዲሰ አበባ